## መልመጃ አንድ÷ ተዋንያን

**Exercise One: Actors**

1. የማትያስ የሥራ ድርሻ ምንድን ነው?
2. አቶ ታምሩ የማን አባት ናቸው?
3. የማትያስ ወላጆች እነ ማን ናቸው?
4. ወ/ሮ ስንዱ የማን ባለቤት ናቸው?
5. የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ምረቃ የተከናወነው የት ነው?
6. አቶ ታምሩ ለምን ደነገጡ?
7. ወ/ሮ ስንዱ ለምን ማትያስ ላይ ራሳቸውን ይዘው አፈጠጡ?
8. ማትያስ ለምን መኪና ያጥባል?
9. ተምሮ እንዳልተማረ የሚሉት ማንን ነው?
10. ማትያስ የናቱን ሕይወት ለማዳን ምን ማድረግ ነበረበት?

## መልመጃ ሁለት÷ምንባብ ÷ትክክለኛውን መልሰ ከ ሀ÷ ለ እና ሐ  ምረጡ

**Exercise Two:** **Reading Comprehension. Choose the right answer between A, B, and C.**

1. ትዕይንቱ የተካሄደው የት ነው?

ሀ. ቤት ውስጥ

ለ.  ሜዳ ላይ

ሐ. ከመንገድ ዳር

2. መኪና የሚያጥቡት እነማን ናቸው?

ሀ. ሽማግሌዎች

ለ. አሮጊቶች

ሐ. በወጣትነት እድሜ ያሉ

3. ባልዲ ማለት

ሀ. ሰሃን ማለት ነው

ለ. ኩባያ ማለት ነው

ሐ. ውሃ መያዣ ከፍ ያለ ዕቃ ነው

4. በድንጋጤ ደርቆ መቆም

ሀ. እንቅስቃሴ የሌለበት በአንድ ሥፍራ መቆም
ለ. ረጋ ብሎ መራመድ

ሐ. መልሱ አልተሰጠም

5. በዩኒቨርስቲ ምረቃ ጊዜ ተማሪዎች

ሀ. ወንበራቸው ላይ በዝምታ ይቀመጣሉ

ለ. ደስተኛ አይደሉም

ሐ. መለዮአቸውን አውልቀው ወደ ጣሪያ ይወረውራሉ

6. ባለቤት ማለት

ሀ. ሚስት ማለት ነው

ለ. ባል ማለት ነው

ሐ. ሁለቱም ትክክል ናቸው

7. “መለስ ብሎ አየ” ሲል ምን ማለት ነው?

ሀ. ደህና ሁኑ ማለት ነው

ለ. ወደ ፊት ተመለከተ ማለት ነው

ሐ. ወደ ኋላ ዞሮ ተመለከተ ማለት ነው

8. “ ዓይኖቻቸውን ከአንድ ቦታ ተክለው” ማለት

ሀ. ተዝናንተው እየተጫወቱ ነው ማለት ነው

ለ. አኩርፈው ቁጭ ብለዋል ማለት ነው

ሐ. ዓይናቸው አይንቀሳቀስም ማለት ነው

9. ኮሞዲኖ ምንድን ነው?

ሀ. ወንበር

ለ. ጠረጴዛ

ሐ. ዕቃ ማስቀመጫ

10. እንባ ቀደማቸው ማለት

ሀ. እንባ ፈጠናቸው

ለ. እየሳቁ ነበር

ሐ. መልሱ የለም

## መልመጃ ሦስት፥ በክፍል ሀ ያሉትን ቃላት ወይም አባባሎች ከክፍል ለ ጋር አዛምዱ

**Exercise Three: Match these words or expressions in column A with their equivalent in column B.**

| አምድ ሀ<br>**Column A** | አምድ ለ<br>**Column B** |
|---|---|
| 1. ዝቅተኛ ደረጃ | ሀ. ማመስገን |
| 2. ኮሞዲኖ | ለ. እንባ ማፍሰስ |
| 3. መደባለቅ | ሐ. መሀይምነት |
| 4. መመረቅ | መ. ማግኘት |
| 5. ማልቀስ | ሠ. ዕቃ መደርደሪያ |
| 6. ትዝብት | ረ. መገረም |
| 7. አለመማር | ሰ. ከፍተኛ ደረጃ |
| 8. መውረስ | ሸ. ከቤተሰብ/ ከዘመድ ማግኘት |
| 9. ድህነት | ቀ. ማጣት |
| 10. ሃብታምነት | በ. አንዱን ከአንዱ ጋር ማዋሃድ |

## መልመጃ አራት፥ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን ሙሉ

**Exercise Four:** **Fill in the blanks by using words from the glossary**

1. በድንጋጤ__________ ከቆሙበት ቦታ ቀሩ::

2. ስንዱ ከአጠገባቸው ደርሰው__________ ::

3. ታምሩ__________ ከሃሳባቸው ባነኑ::

4. ስንዱ ግራ ___________::

5. የቀኝ እጃቸውን በመዘርጋት የሌባ ጣታቸውን ___________ ::

6. ስንዱ ወደ ማትያስ __________ ይመለከታሉ::

7. ማትያስ ከሥራው ላይ __________ ይታያል::

8. ስንዱ ክፉኛ ደንግጠው በሁለት እጆቻቸው እራሳቸውን ይዘው ከማትያስ ላይ

___________ ::

9. ማትያስ መኪናውን __________ ነው::

10. የያዘውን ማጠቢያ እየጣለ __________ ብሎ ተመለከተ::

## መልመጃ አምስት፥ የተሰመሩትን ቃላት በተመለከተ ጥያቄዎች ጠይቁ

**Exercise Five:** **Ask questions corresponding to the underlined words**

1. ዝቅተኛ ደረጃ
2. ከፍተኛ ደረጃ
3. አለ ደረጃ
4. ወጪ
5. ገቢ
6. ድካም
7. መፈለግ
8. ችግር
9. መርሳት
10. መማር

## መልመጃ ስድስት፥የማዳመጥ ምንባብ፥ ውይይቱን ተመልከቱና በእያንዳንዱ መሥመር ላይ ያላችሁን አስተያየት ስጡ።

**Exercise Six:** **Listening comprehension. Watch the conversation and comment each line**

ታምሩ - ከላይ በድንጋጤ ደርቀው ከቆሙበት ቦታ ፊታቸው ከቅርበት እየራቀ መታየት እንደ ጀመረ ...

ስንዱ - ከአጠገባቸው ደርሰው እየቆሙ ባለቤታቸውን በአንድ እጃቸው ይነቀንቋቸዋል

ታምሩ - በድንጋጤ ከሃሳባቸው በመባነን ዓይኖቻቸውን ከልጃቸው ላይ በመንቀል ወደ ባለቤታቸው ዞረው ያያሉ።

ስንዱ - ደንግጠው ግራ በመጋባት እያዩአቸው ምን ሆኑ?

ታምሩ - እንዳይደንግጡ ምንም ሳይናገሩ የቀኝ እጃቸውን በመዘርጋት የሌባ ጣታቸውን በመቀሰር ወደ ማትያስ ያመለክታሉ ።

ስንዱ - ወደ ማትያስ ዞረው ይመለከታሉ

ማትያስ - በወላጆቹ አመለካከት ወደ እነሱ ሳያይ ከሥራው ላይ እንዳተኮረ ይታያል

ስንዱ - ክፉኛ ደንግጠው በሁለት እጆቻቸው እራሳቸውን ይዘው ከማትያስ ላይ እንዳፈጠጡ ውይ!!!

ማትያስ - መኪናውን እያጠበ ድንገት መለስ ሲል ወላጆቹን ይመለከትና ክፉኛ ደንግጦ የያዘውን ማጠቢያ እየጣለ ቀና ብሎ ሲመለከታቸው ፊቱ ከርቀት እየቀረበ ይታያል።

## መልመጃ ሰባት፥ አዎንታ ወይም አሉታ ጥያቄዎች

**Exercise Seven: yes or no questions**

| | አዎን | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. የማትያስ የሥራ ድርሻ መኪና ማጠብ ነው | | |
| 2. አቶ ታምሩ የከበደ አባት ናቸው | | |
| 3. የማትያስ ወላጆች ወ/ሮ ስንዱና አቶ ታምሩ ናቸው | | |
| 4. ወ/ሮ ስንዱ የአቶ አፍሬም ባለቤት ናቸው | | |
| 5. የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ምረቃ የተከናወነው ሆቴል ነው | | |
| 6. አቶ ታምሩ በልጃቸው የሥራ ሁኔታ ተናደዋል | | |
| 7. ወ/ሮ ስንዱ በማትያስ ሥራ አልተበሳጩም | | |
| 8. ማትያስ የቢሮ ሠራተኛ ነው | | |
| 9. ተምሮ እንዳልተማረ የተባለው ማትያስ ነው | | |
| 10. ማትያስ የናቱን ሕይወት ለማዳን መኪና ማጠብ ነበረበት | | |

## መልመጃ ስምንት፥ ተቃራኒ የሆኑትን ቃላት በመልመጃው ውስጥ ፈልጉ

**Exercise Eight: Find the antonyms of these words in the text.**

1. ከፍተኛ ደረጃ
2. ሀዘን
3. ባለ መኪና
4. እየተቀመጡ
5. ከቅርበት
6. ማቆሸሽ
7. አዲስ እቃ
8. እየቀረበ
9. ገንዘብ መቆጠብ
10. መዋረድ

## መልመጃ ዘጠኝ፥ ውይይቱን በራሳችሁ አባባል/ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉ

**Exercise Nine: Summarize the dialogue in your own words.**

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

## መልመጃ አስር፥ ኪነት መሥራት፡፡ ኪነቱን ተለማምዳችሁ የከተማውን አማርኛ በመጠቀም ዝግጅት አቅርቡ፡፡ ይህ ዝግጅት ባህሉን፥ አቀራራረቡን እና ሌሎች የቋንቋው ስልቶች እንዲገቡ ያስፈልጋል፡፡

**Exercise Ten: Role play:** Rehearse and perform the skit by using urban Amharic.

Be mindful to reflect the local culture, gestures and other kinesics aspects of language